FAMIS

የቨርጂንያ የጤና መድን ፕሮግራም ለሕጻናት

*ልጆችዎ የሚገባቸው ጥበቃ የእርስዎ አቅም በሚፈቅደው ክፍያ!*

## FAMIS እና Medicaid ለልጆች ምንድናቸው?

**FAMIS** የቨርጂንያ የጤና መድን ፕሮግራም ለሕጻናት ነው። የጤና መድን ለሌላቸው ሕጻናት ጥራት ያለው የጤና አገልግሎቶችን ተደራሽ ያደርጋል። **Medicaid ለልጆች** በተጨማሪም ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ወይም ገቢ በሌላቸው ቤተሰቦች ውስጥ ላሉ ሕጻናት፣ ሕጻናቱ የጤና ሽፋን ቢኖራቸውም እንኳን ጥሩ ጥቅማጥቅሞችን ያቀርባል። ለሽፋን በሚያመለክቱ ጊዜ፣ ልጅዎ ለ**FAMIS** እና ለ **Medicaid ለልጆች** ለሁለቱም ታሳቢ ይደረጋል።

## ሽፋን የሚሰጠው ምንድነው?

- የሐኪም ጉብኝቶች
- የሆስፒታል እና የድንገተኛ ሕክምና ክብካቤ
- ጤንነቱ የተጠበቀ ልጅ እና ጤንነቱ የተጠበቀ ጨቅላ ምርመራዎች
- ክትባቶች
- በትዕዛዝ የሚገዙ መድሃኒቶች
- የላቦራቶር ምርመራዎች እና ራጅ
- የዓይን እና የጥርስ ጤና ክብካቤ
- የአዕምሮ ጤና ክብካቤ
- እና ሌሎችም ...

በ**FAMIS** ወይም **Medicaid ለልጆች** በቤተሰብዎ ላይ ወርሃዊም ሆነ ዓመታዊ ክፍያዎች አይኖሩም። በ**FAMIS** ውስጥ ለተመዘገቡ ሕጻናት፣ ለተወሰኑ የሕክምና ክብካቤዎች ትንንሽ የጋራ ክፍያዎች ($2 ወይም $5) አሉ።

## መስፈቱን የሚያሟላው ማነው?

ሕጻናት ለ**FAMIS** ወይም **Medicaid ለልጆች** ብቁ የሚሆኑት የሚከተሉትን መስፈርቶች ካሟሉ ነው፡-

- በቨርጂኒያ ውስጥ የሚኖሩ እና ከ19 ዓመት በታች ከሆኑ
- የዩኤስ ዜጎች ከሆኑ (አንዳንድ ዜጎች ያልሆኑ መስፈርቱን ያሟላሉ) የወላጆች ዜግነት ግምት ውስጥ አይከተቱም
- የተወሰኑ የገቢ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ (ቀጣዩን ሰንጠረዥ ይመልከቱ)

## FAMIS የገቢ ገደቦች (ጠቅላላ*)

| የቤተሰብ መጠን | ወርሃዊ | ዓመታዊ |
|---|---|---|
| 1 | $2,491 | $29,889 |
| 2 | $3,369 | $40,426 |
| 3 | $4,247 | $50,963 |
| 4 | $5,125 | $61,500 |
| 5 | $6,004 | $72,037 |
| **ተፈጻሚ የሚሆነው ጃንዋሪ 20፣ 2023። የገቢ ገደቦች በየዓመቱ ይታደሳሉ። ለተጨማሪ መመሪያዎች ይደውሉ።* | | |

የተመዘገቡ ሕጻናት ያሏቸው የመንግስት የፍልሰተኛ ቤተሰቦች **FAMIS** ወይም **Medicaid ለልጆች** መቀበል በቤተሰቦች የዩኤስ ዜግነትን የማግኘት ሂደት ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም።

## እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

ለ**FAMIS** ወይም **Medicaid ለልጆች** ማመልከት ቀላል ነው።

የሚያስፈልግዎ ወደ ነጻ ስልክ መስመር 833-5CALLVA መደወል ብቻ ነው። ተርጓሚዎች ይገኛሉ። ወኪሎቻችን፣ እርስዎ የሚመርጡትን ቋንቋ ከሚናገር ሰው ጋር ያገንኙዎታል።

ወይም በመስመር ላይ ለማመልከት ወደ commonhelp.virginia.gov በመለያ ይግቡ

በተጨማሪም ለእርስዎ አካባቢያዊ የማኅበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ ማመልከት ይችላሉ።

በሚያመለክቱ ጊዜ የሚያስፈልጉዎትን የሰነድ ዝርዝሮች ለማግኘት፣ www.coverva.org ን ይጎብኙ እና በተግብር ገጽ ላይ ጠቅ ያድርጉ። ልጆቹ የዩኤስ ዜጎች ካልሆኑ የፍልሰተኝነት ሁኔታቸውን ማረጋገጫ ማቅረብ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። ልጅዎ የዩኤስ ዜጋ ከሆነ/ች፣ በማመልከቻው ላይ የልጅዎን የማኅበራዊ ደህንነት ቁጥር እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ።

FAMIS
Covering Children With Affordable Health Insurance